ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshweg...

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara's organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ቅዳሜ፣ ሰኔ ፳፣ ፪ሺ ፲፪ ዓ.ም. (June 27, 2020) ቅጽ ፯ ቁጥር ፳*

# ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ፅጌ ስለምን ተገመገሙ?

በለስ ቀንቷቸው ወያኔ፣ ሻቢያና ኦነግ በጥምረት ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሩበት ጊዜ ጀምሮ የዐማራ ህዝብ እንደፈረደበት አይዞህ ባይ፣ እንባ አባሽ ወገን አጥቶ እስከ አሁኑ ሰዓት ድረስ በጅምላ በአሰቃቂ ሁኔታ ይገደላል፣ ይቃጠላል፣ ይፈናቀላል፣ ይሳደዳል። ወያኔም በዐማራው ግዛት ላይ አዛዥ ናዛዥ ሁና የትግራይ ወሰንተኛ የሆኑትን የዐማራ ሕዝብ አጽመ-ርስት ቦታዎች ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ጠለምት እና ራያ ለራሷ ክልል በኃይል ስትጠቀልል ሌሎቹን ግዛቶች ከሸዋ ከጎጃም ከወሎ እንደፈለጋት ለሌሎች በመቸር ለሱዳን ሳይቀር የጎንደርን መሬት ቆርሳ በመለገስ ዐማራን ርስት አልባ አድርጋ አመቻቸች። በዚህ ሁሉ አከላለልና የጥፋት ስራ ወንጀሉን ለመሸፈን ስሙን የሚቀያይረው የቀድሞው "ኢሕድን" አሁኑ ብአዴን/ አዴፓ ብልፅግናም የዝሆኑን ድርሻ ይወስዳል።

ይህ ጉዳይ የመሬት ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ፤ በከፍተኛ ደራጃ የህልውና እና ማነነትን ጥያቄ ነው። ለዚህም እንደማሳያ ዐማራ አያት ቅድም አያቱ ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ሁሉ መጤ እየተባለ ተጨፍጭፏል፣ አሁንም ጭፍጨፋው እንደቀጠለ ነው። ከዐማራ በተነጠቁት አካባቢዎች በሙሉ በብሔራዊ ቋንቋ አማርኛ ማልቀስና መዘፈን የህይወት ዋጋ ያስከፍላል። ዐማራ በብዛት የሚኖርበት የቀድሞው የጎጃም ክፍለ ሀገር መተከል አውራጃ ጉሙዝ ውስጥ ዐማራ መግደል ነውር አይደለም። ወያኔ ወደ ትግራይ በጉለበት ባጠቃለላቸው ግዛቶች ግፍን ከመፈፀሙ በተጨማሪ ባሰለጠናቸው የቅማንት ኮሚቴ ነፍሰገዳዮች ዐማራ በክልሉም ይገደላል። የቅማንት ኮሚቴ ይህን የሚያደርጉት በሕዝብ ብዛታቸውና በጉልበታቸው ተማምነው እንዳይባል የቅማንት ሕዝብ ቁጥር በአጠቃላይ ከ 500 ሺህ አይበልጥም። በእዚያ ላይ የቅማንት ሕዝብ ከዐማራ ወገኑ ጋር ምንም አይነት ቅራኔ የለውም። ችግሩ ግን በለየለት ፀረ-ዐማራው ወያኔ የሚዘወረው የፓለቲካ ሸፍጥ ነው።

ለዚህ ሁሉ በደል ተባባሪ የሆነው ደግሞ የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም እንዲሉ የቀድሞው ብአዴን የአሁኑ አዴፓና ብልፅግና ነው። የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚንስትር ታምራት ላይኔ እራሱን የዐማራ ተወካይ ነኝ በሎ ምስራቅ ኢትዮጵያ ወርዶ "ሽርጣም ይልህ የነበረው ነፍጠኛ ዐማራ ልኩን አሳየው" ብዙ ሺህ የዐማራ ተወላጆችን አስጨፍጭፏል። ይህ የሚያሳየው የዐማራን ሕዝብ ሊመሩ ቦታ የሚይዙት የዐማራው ገዥዎች ለዐማራ ሕዝብ ስነ ልቦና የማይመጥኑ ብቻ ሳይሆን ዐማራ ሲጠፋ እንደሚደሰቱ የታምራት ላይኔ የዐማራን ጨፍጭፋት ጥሪ ማሳያ ነው።

የብአዴን የቀደመ ጥፋቱ ተዘርዝሮ ባያልቅም፣ ወደ አዲሱ አዴፓና ዋናው ርዕስ እንመለስና ለውጥ ተብየው ከመጣ በኋላ ሁሉም ሰው የቀደመ ቁስሉ ሳይሽር ኢሕአዴግዎች "ገምተን በስብሰን ነበር" ሲሉ ሕዝቡ ያለፈውን በደል ትቶ ወደፊት ለማየት ሞክሮ ነበር.። አዴፓም ዐማራን "ልሀጫም" እያሉ ሲመፃደቁ የነበሩት ደናቁርት ሹማምንት በፍርድ መጠየቁ ቢቀር ከስልጣን ሳይነሱ ስራውን ቀጠለ። የሚያሳዝነው የይስሙላ ለውጥ መጣ ከተባለ ውዲህም ታምራት ላይኔ ተፅፅቶ የዐማራን ሕዝብ ይቅርታ እንዲጠይቅ እንደማድረግ አዴፓ በካባ አሸሞነሞነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሚለኒየም አዳራሽ ታምራት ላይኔን ሲጋብዙ ድምፃቸውን ያወጡበት ቅላፄ ጠቅላይ ሚኒስትር ቀርቶ ተራ ካድሬ እንኳን ብዙ ህዝብ በተሰበሰበበት የማይጠቀምበት ድምፅ ስለነበረ ዶ/ር አብይ በዚያ የድምፅ ቃናቸው ብቻ የብዙዎችን እምነት እንዲያጡ ሁኗል። በኋላም ጠቅላይ

ሚኒስትሩ የሙት ደም እየጠራቸው በየአደባባዩ ጄኔራል አሳምነውን እያነሱ ከእስር አስፈትቸው፣ ገንዘብ ከፍየለት፣ ቤቱን አስመልሸለት እያሉ የተናገሩት ሁሉ ሀሰት ከመሆኑም በላይ፣ የተናገሩት ከእውነታው ጋር አለመገጣጠም ለተናገሩት ሁሉ እምነትን እንዳይቸሩ አስተዋፅኦ አድርጓል።

አስተዋዩ የዐማራ ሕዝብ እየታዘበ ድጋፉን ቢቀጥልም አዴፓ አቻነቱን ትቶ በቀደመው አሽከርነት ማንነቱ አሁንም የኦዴፓና የአብይ አህመድ አገልጋይ በመሆን እነሱን የሚያስደስተውን ብቻ ማድረጉን ተያይዞታል።

ዶ/ር አብይ አህመድ ደሴ ላይ ስለልማት ሲጠየቁ ”...ክልል 147 ሚሊዮን ለክልሎች ሰጠን። ለልማት ለውሀ ለመብራት ...ያን ብር ወስደው ሚሊሽያ የሚቀልቡበት ከሆነ ከየትም ልናመጣ አንችልም ማለት ነው...” ማለታቸው የሚታወስ ነው። ይህ ሁሉ ከበባ ያለበት የዐማራ ክልል ገና በዳዴ የሚሄደውን የአንደኛ ዙር የልዩ ኃይል ስልጠናውን በዚህ መንገድ ተቃውመው ያወገዙትና እንደነውር የቆጠሩት ዶ/ር አብይ ያለ ይሉኝታ የኦሮሞ ክልል ግን በጀት ሳይቸግረውና ተቃውሞ ሳይገጥመው 30, (ሰላሳ) ዙር ልዩ ኃይል እያሰለጠነ እንዲያስመርቅ አደረጉ። በስንት ወቀሳና ነቀፋ የሰለጠኑት የዐማራ ልዩ ኃይል ተመራቂዎች ሲመረቁ በስነሥርዓቱ ላይ ዶ/ር አብይ ጋር ደሴ የሰነበቱት የዐማራ ክልል ሹማምንት እንዲገኙ በክብር ቢጋበዙም ”የዐማራ ብሄረተኝነት ያሰጋኛል” ያሉት የዶ/ር አብይ ተባባሪ በመሆን መገኘት በሚገባቸው በዚህ ሥነ-ሥርዓት ላይ አልተገኙም።

ለወያኔ ውድቀት ትንቅንቅ ላይ እንደነበሩ የሚነገርላቸው የዐማራው ክልል ርዕስ መስተዳደር ዶ/ር አምባቸው መኮንን ”የዐማራን ሕዝብ መብትና ጥቅም አሳልፈን ለመስጠት ከማንም ጋር አንደራደርም” ባሉበት አፋቸው የዐማራን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ለኦሮሙማ ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ ንግግር አምቦ ላይ ተናገሩ። እንዲህም አሉ። “አዲስ አበባን በተመለከተ ሕግ መንግስቱ ያስቀመጠውን የሚሸራርፍ አቋም ማንም የለውም። የኦሮሚያ ክልል ልዩ ሕገ መንግስታዊ መብት አለው። ልዩ ሕገ መንግስታዊ መብቱ እንዲከበርለት ደግሞ እኛም እንታገላለን”። በእርግጥ ዶ/ር አምባቸውም በእዚህ ጉዳይ ከህዝብ ከፍተኛ ተቃውሞ ሲደርስባቸው ምን ለማለት እንደፈለጉ ትንታኔ የሰጡበትንም አይተናል።

ዐማራው ችግሩ ከለውጡ ወዲህም ተባብሶ ቀጠለ። ዐማራው ራሱ ክልልህ ተብሎ በተከለለት ክልል ከሚሴና ጎንደር ሳይቀር በኦነግና በወያኔ ረዥም እጅ እየታገዘ ጭፍጨፋው ቀጠለ። ደረጃውን የጠበቀ የመከላከያ ልብስ የለበሰ የኦነግ ሰራዊት በከሚሴ በአጣየና በአካባቢው ብዙዎችን ጨረሰ፣ ቤተክርስቲያን አቃጠለ። ከየክልሉ መድረሻ ቢሶቹ ”ዐማሮች ናችሁ” ስለተባሉ ተወልደው ካደጉበት ተፈናቅለው ሜዳ ላይ ተበተኑ። ከሞት የተረፉት ተፈናቃዮች ዐማራ ክልል ያሉት ጥለው አይጥሉንም ብለው ተንገላተው ቢመጡም አዴፓ በስማቸው 8,000,000 (ስምንት ሚሊዮን) ብር ሰብስቦ መጠለያ እንኳን ሳይሰራላቸው እስከ አሁን በቁር፣ በፀሀይና በዝናብ ሲንገላቱ ሁለት ዓመት አለፋቸው። አሁንም ክረምት እየገባ ስለሆነ የተፈናቃዮቹ ስቃይ ይቀጥላል። ዐዴፓን የዐማራ ወገንተኛ መሪ ብሎ ማሰብ ይከብዳል።

አሁን ደግሞ አዲስ ክስተት ባያካትቱም ጄኔራል ተፈራ ማሞ የሰኔ 15ቱን ክስተት በሚዲያ ቀርበው ከወራት በፊት ሲናገሩ የሰማነውን ያንኑ በድጋሚ በጽሑፍ አስፍረው ለምን እንዳስነበቡን ባይገባንም ግምገማው ምን ምን ያካተተ እንደነበረ አለመግለፃቸው ግን ዛሬም ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅትና የዐማራ ሕዝብ መልስ ያላገኘለት ጥያቄን አስከትሏል። ምክንያቱም ሕዝቡ ጄኔራሉን ዘጠኝ አመት በወያኔ ፅኑ እስር ቤት በእስራት የቆዩ፤ በእስር በነበሩበት ጊዜም አብረዋቸው ታስረው የነበሩት እነጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ በፆምና በፀሎት ስጋዊ ሰውነታቸውን ገትተው የሚኖሩ፤ የዚህ ዓለም ብልጭልጭ ኑሮ የማያታልላቸው መሆናቸውን ስለመሰከሩ፤ ጄኔራል ተፈራም ”ጄኔራል አሳምነው በባህሪው ሃይማኖተኛ ነው።. ..በግሌ ለሃይማኖቱ በነበረው ቀናዊ ስሜት መንፈሳዊ ቅናት ያሳድርብኝ ነበር”፣ በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ስለሰጡ፣ ጄኔራሉ ከእስር ከተፈቱም ቀሪውን ጊዜያቸውን የዐማራን ሕዝብ በቅንነት ለማገልገል መወሰናቸውን ስለሚያውቅና በተግባርም ደፋ ቀና ሲሉ ስላየ ጄኔራል አሳምነው ፅጌን እንደ ተራ ነፍሰገዳይ ወንጀለኛ ማየት ይከብደዋል።

ስለዚህ ሕዝብ እውነቱን የማወቅ መብት ስላለው ቢያንስ ቢያንስ ከታች የተዘረዘሩት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

ጥያቄዎቹም፥

1. ከደሴ ሲመለሱ ዶ/ር አብይ በራሳቸው ተነሳሽነት ለነዶ/ር አምባቸው ልዩ ጠባቂ የሰጧቸው ለምን ነበር? የክልሉ ሰልጡን ጠባቂዎች ስለማይተማመን? ወይንስ ታማኝ ተብለው ከፌዴራል የተላኩት ልዩ ጠባቂዎቹ ሌላ ተልዕኮም ነበራቸው?
2. ጀኔራል ተፈራ ማሞ የሰኔ 15ን ፍጅት አስመልክቶ እንደነገሩን ለጀኔራል አሳምነው ኦፐሬሽኑን የመራለት ከቤተመንስግስት ተጣልቶ የወጣ ሻምበል ማማል ጌትነት ነበር። ኦፐሬሽኑን ከመራ በኋላ ተሰወረ፣ ሰውየው ከወራት በኋላ ድሬድዋ ከተማ ተይዞ በስህተት ነው ተብሎ ተፈታ ብለውናል። ያ ሻምበል ማማል ጌትነት የተባለው ሰው ማነው? ተልእኮውስ ምን ነበር? ለምንስ ከተያዘ በኋላ መልሶ ተለቀቀ?
3. ሰኔ 15 ባለስልጣናቱና ልዩ ኃይሉ ከተገደሉ በኋላ፤ ጄኔራል አሳምነው ከመገደላቸው በፊት አንድ የጄኔራል አሳምነው አጃቢ የነበረ የልዩ ኃይል አባል ለማተቡ የፃፈው ረዘም ያለ ጽሑፍ ተበትኖ ነበር። ከጽሑፉ በጣም ትኩረትን የሳበው ግን፤ **ጄኔራል አሳምነው ተጠርቶ ባለስልጣኖቹ የተሰበሰቡበት ቦታ ስንሄድ በር ላይ የጄኔራል አሳምነው ገፅታ ያለው ጭምብል (ማስክ) አድርጎ የቆመ፣ ቁርጥ ጄኔራል አሳምነውን የሆነ ሰው ባየን ጊዜ እኛም ጄኔራል አሳምነውም ሁላችንም ደነገጥን።** የሚለው ነበር። መረጃ አይናቅምና አዴፓ ከጥቅመኛ አዴፓ አባላት ጋር ተመካክሮ በጄኔራል አሳምነው ስም የተቀነባበረ፤ የዐማራን ባለስልጣናት የማስወገድና እነዶ/ር አምባቸውን ሟች፤ እነጄኔራል አሳምነውን ገዳይ በማድረግ፤ ዐማራ እንዳይግባባና እስከመጨረሻው ሆድና ጀርባ ሆኖ እንዲኖር የሚያደርግ ኦፐሬሽን ተፈፅሞ ቢሆንስ?
4. የባልዳራስ አመራሮች ሰኔ 15 ከአዲስ አበባ ወደ ባህርዳር ለመሄድ ባሰቡበት ሰዓት እንዳይሄዱ በተደጋጋሚ ጉዞው እየተሰረዘ የተራዘመው ለምን ነበር?
5. ለምን ከአርብ ሰኔ 14 ቀን ምሽት ጀምሮ ከባሕር ዳር ከተማ የሚያስወጡት ኬላዎች በሙሉ እንዲዘጉ ሆኑ?
6. ግድያው ከሰአት በኋላ 11 ሰዓት ላይ ከመፈጸሙ ቀደም ብሎ፣ በአውሮፕላን በረራ ባሕርዳር አውሮፕላን ማረፊያ የነበሩ የባልደራስ አመራሮችና ሌሎችም መንገደኞች ከእኩለ ቀን ጀምሮ ከአውሮፕላን ማረፊያ እንዳይወጡ የተከለከለው ልምን ነበር?
7. የአዲስ ፎርቹን ጋዜጠኛ የሆነችው (ጋዜጠኛ ፋሲካ) ግድያው ከተፈጸም ከሁለት ሰአት በኋላ ጄኔራል አሳምነውን በስልክ አግኝታቸው መፈንቅለ መንግስት ተደርጓል ተብሎ በዜና ስለቀረበው ጠይቃቸው፤ ጄኔራሉም ስለመፈንቅለ መንግስቱ እንደማያውቁና ጉዳዩን ለማጣራት ወደ ክልሉ አስተዳደር ጽ/ቤት እየሄድኩ ነው፣ አጣርቼ አደውልልሻለሁ ብለዋት ነበር። የስልክ ንግግሩን በሙሉ እንደቀረጸችው ለሚዲያ አስታውቃ ነበር። ይህ የድምጽ ማስረጃ ለሕዝብ ይፋ አልሆነም፤ ጋዜጠኛዋም ከዚያ ወዲህ ድምጿ ተሰምቶ ለምን አያውቅም?
8. የጄኔራል ሰአረ ባለቤት (ኮለኔር ፅጌ አለማየሁ) ከሰኔ 15ቱ ጋር በተገናኘ ሁኔታና ስለባለቤታቸው አሟሟት መሳፍንት የተባለው ወታደር በጄኔራል አሳምነው ፅጌ ታዝዤ ነው ጄኔራል ሰአረን የገደልኳቸው ብሎ የሰጠውን ቃል አልቀበለውም ማለታቸውለምን ይሆን?
9. ከላይ የቀረቡት 5 ጥያቄዎች አካባቢን የሚቃኝ ሲሆን ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት "**ጄኔራል አሳምነው ለምንና እንዴት ተገመገሙ? ግምገማው በአራት ኪሎ ቤተመንግስት ለምን ተጀመረ?"** የሚለውን ግን አዴፓን በቀጥታ የሚመለከት ቁልፍ ጥያቄ ሆኖ አግኝቶታል። ስለዚህ የሁሉም ቁስል እንዲሽርና መተማመን እንዲኖር አዴፓ ግምገማ ውይይቱን በቪዲዮ አስደግፎ ግልፅ ማድረግ ይኖርበታል።

ብርጋዴር ጄኔራል አሳምነው ፅጌ ስለምንና በምን ጉዳይ ተገመገሙ?

- ጄኔራል አሳምነው ከሚመሩት ሠራዊት ጋር ስለማይግባቡ በአመራር ብቃት ማነስ?

- ሴት በመድፈር?
- የሕዝብ ሃብት በመዝረፍ?
- ህብረተሰቡን በመናቅና በማዋረድ?
- ሰብአዊነት የጎደላቸው ስለሆኑ? ወ ዘተ?

ወይስ?

- እረዥም ጦር ባይወጉበትም ያስፈራሩበታል እንዲሉ ልዩ ኃይል ላሰልጥን የአማራን ሕዝብ ከጥቃት እንከላከል በማለታቸው?
- በከሚሴ በአጣየና በቅማንት የዘር ጭፍጨፋ መከላከያና አጥፊዎቹ ለሕግ እንዲቀርቡ ገፍተው ስለሄዱ?
- ከዐማራ ወጣቶችና ከፋኖ ጋር በትብብር በመስራታቸው?
- ዐማራ የተጋረጠበትን አደጋ ለዐማራ ሕዝብ በማሳወቃቸው? የሚሉት ሲሆኑ
- ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አንድ ዓመት ሙሉ ሕዝብ እየወተወተ ግድያው በገለልተኛ ወገን እንዲጣራ አለመደረጉ ለምን እንደሆነ? ጄኔራል አሳምነው አጥፍተዋል ከተባሉ በቁጥጥር ስር አውሎ ጉዳዩ በሕግ ሊታይ ሲገባው ለምን ተገደሉ? በማንና እንዴስት ተገደሉ? የሚሉትም ጥያቄዎች መልስ የሚሹ እንደሆኑ በፅኑ ያምናል።

የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ፤ ሕዝብና ቤተሰብ የግድያዎቹ መንስኤዎች፣ የግድያው ፈጻሚዎችና የግድያው ዋና መሪዎች እነማን እንደሆኑ ሀቁን ማወቃቸው የማይቀር ነው። ነገሩን ግልፅ ለማድረግና ሚችና ገዳይን ለማሳወቅ እንዚህና ሌሎችም ጥያቄዎች በሰፊው መመለስ ይኖርባቸዋል። እውነቱን የሚያጣራ ነጻና ገለልተኛ ኮሚሽን ተቋቆሞ እውነቱ በገሀድ እስኪወጣ ድረስ አውነትም ሆኑ ውሸት እንዚህና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በቋሚነት ይቀጥላሉ።

ይህ ለውጥ አመጣለሁ የሚል መንግስት በእንቆቅልሽነት የቆዩ ብዙ በአዲስ አበባና በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የተፈጸሙ ግድያዎችን አጣርቶ ለሕዝብ የማቅረብ ፍላጎት አለማሳየቱ በጣም አሳዛኝ ነው። ለዚህም ዋናው ተጠያቂ እራሳቸውን የለውጡ አቫጋሪ አድርገው የሾሙት ዶ/ር አብይ አህመድ ናቸው። ስለዚህ ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ተገኝቶ ሕዝብ በተለይም የሟች ቤተሰቦች እውነቱን እንዲያውቁት የማድረግ ሙሉ ኃላፊነት ያለው ዶ/ር አብይ አህመድ የሚመሩት የፌዴራል መንግስት ነው።

በተለይ ይህን አሳዛኝ ግድያ መፈንቅለ መንግስት አድርጎ የፈረጀ መንግስት እውነቱን የማውጣት ግዴታው ግልጽ ሊሆንለት ይገባል። የተለያዩ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻና ውሸቶችን በመደራረብ በሕዝቡ ዘንድ ተአማኒነትን ማግኘት እንደማይቻል በማወቅ፣ የሰኔ 15 የዐማራ መሪዎችን ግድያ፣ ያንንም ተከትሎ የተፈጸሙ ግድያዎችና በተደበሰበሱ ምክንያቶች የተደረጉ እስራቶችን የሚያጣራ ገለልተኛና ከግድያ ተግባሩ ምንም አይነት ግንኙነት የሌላቸው ነጻ አባሎችን የያዘ የአጣሪ ኮሚሽን ባስቸኳይ የፌደራል መንግስት አቋቁሞ የምርመራውን ውጤት ለሕዝብ ያቀርብ ዘንድ ሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት ጥሪውን ያደርጋል።

ይህን የሰኔ 15 ግድያን ተከትሎ በብአዴን / አዴፓ / ብልጽግናና ሌሎች ዐማራ-ጠል ኃይሎች እየተደረገ ያለውን ዐማራውን በመንደር የመከፋፈል ሴራ፤ ጄኔራል ተፈራ "አዴፓ ለማንና ለምን መስራት እንዳለበት በውል ያልለየ፣ በአውራጃዊነት ፓለቲካ የተጠላለፈ፣ አራሙቻ አመራር በውስጡ ያቀፈ ነው" እንዳሉት አራሙቻው ተነቅሎ እውነት እሲወጣ ድረስ የዐማራ ሕዝብ ትግሉን ይቀጥላል። በዚህ አጋጣሚ ዐማራው ሴራውን በተባበረ ክንዱ እንደሚያከሽፍውና አንድነቱን እንደሚያጠነክር ወዳጅም ጠላትም ሊያውቀው ይገባል እንላለን።

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለዐንድ ዐማራ!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!